ሞዓ አንበሳ

MOA ANBESSA

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ፤ ነጻነት ፤ አኩሪ
ታሪክና ባሕል የሚያመለክተው ሞዓ አንበሳ በዓለም
ሕብረተሰብ ዘንድ ልዩ አክብሮትና ግርማ ሞገስ
ሲያሰጠን የኖረ ልዩ ምልክታችን መሆኑን ነው ።

የነጻነታችን አርማ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማችን
የክብራችን መሠረት ፥ የልምላሜ ፤ የሰላምና የመስ
ዋዕትነት ብሥራት ይዞ የሚጓዘው አንበሳ ሂደቱ
ለዘመናት የሚቀጥል የኢትዮጵውያን ሁሉ መለያ
ነው ።

ዛሬም ሆነ ጥንት በዘውድ ጥላ ስር የኖሩ የለ
ሙትም ሆኑ በልማት ላይ የሚገኙ አገሮች ለታሪ
ካቸውና ለአንድነታቸው መጠበቅ ሲሉ ዘውዱን
በልዩ አክብሮት ይንከባከቡታል ይጠብቁታልም ።
ለምሳሌ ከአውሮፓ እንግሊዝ ፤ የእስካንዲኔቪያን
አገሮችና ከእስያም ጃፓንን ሌሎችንም የአፍሪቃና
የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች መጥቀስ ይቻላል

በተለይ እንግሊዝና ጃፓን ዛሬ ዓለምን በልማትና
በሥልጣኔ ከሚመሩት አገሮች ቀደምት ሥፍራ ይዘው
ከሚገኙት መሐል ናቸው ። በርግጥም ዘውድ ለልማ
ትም ሆነ ለፖለቲካና ለማህበራዊ ኑሮ ውጤታማነት
የሚጫወተውን ሚና ከነሱ ማመሳከር ይቻላል ።

እውነተኛ ሥልጣኔና ልማት የታሪክ ተጻራሪ ሳይ
ሆን የታሪክ የበላይነትን ተቀብሎ የሚቀጥለውንም
ባህል አዳባሪ በመሆኑ እንደሌሎቹ ብርቅና ድንቅ
ቅርሶቻቸው ሁሉ የዘውድ ቅርሳቸውንም በጥንቃቄ
ይጠብቁታል ።

በመጠበቃቸውም በአጭሩ የጃፓንን ታሪክ ስንመ
ለከት ለዛሬው የቴክኖሎጂ እድገት አንድነት ልማ
ትና ሥልጣኔ የሜጂ ሥርወ መንግሥት ታላቅ
አስተዋጽኦ ማበርከቱን ከታሪክ መዛግብትና አሁን
ከሚገኙበት አዎንታ ለማመሳከር አያዳግትም ።

ከዛሬ ፲፯ ዓመት በፊት የፖለቲካ የኢኮኖሚ
የማኅበራዊና የባህል እድገታችን መለስ ብለን ስንቃኝ
እድገቱ በአምባገነን ወታደራዊ አገዛዝ ባይገታ ኖሮ
የት ሊደርስ ይችል እንደነበር በወቅቱ የነበርን ሁሉ
ማስረጃ የምንሰጥበት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን መላው
የዓለም ሕዝብ በቁጭት የሚመለከተው ነው ።
በልመና መታወቃችን ቀርቶ ቢያንስ በአጼ ኃይለ
ሥላሴ የዘውድ ዘመን የነበረውን የኑሮ ደረጃ ዛሬ
አግኝተነው ቢሆን ኖሮ ምንኛ በታደልን ነበር ።
ያም ብቻ አይደለም የሀገራችን ሰላምና አንድነት
ተከብሮ ገናናና ታሪካዊ ሥፍራውን ሳይተው ደማቅ
ግርማውን እንደያዘ ፀንቶ በኖረ ነበር ።

ክቡራትና ክቡራን ኢትዮጵያውያን ሆይ !!

አባቶቻችን ባቆዩልን የዘውድ ጥላና የታሪክ ቅርሳችን
ሥር ተሰባስቦ በአንድነትና በነፃነት ለመኖር እንደ
እንግሊዝና እንደጃፓን የሥልጣን ገደቡ በሕግ ከተ
ወሰነ ሕግ መንግሥታዊ የዘውድ አስተዳደር የተሻለ
የሰላምና የብልጽግና ምን ዋስትና ይኖረናል ? ሕገ
መንግሥታዊ ዘውድ ሲባልም የሕዝቦችና የሕግ ልእ
ልና የሚከበርበትና ሕዝቦችም በሚመርጡት ፓርቲ
የሚተዳደሩበት ሆኖ ኢትዮጵያ በዘውድ መኖሯን
የሚያመለክት የአንድነትና የሰላም ማረጋገጫ ልዩ
ታሪካዊ ምልክት (መታወቂያችን) ነው ።

የዘውድ በትክክለኛው የክብር ሥፍራ መቀመጥ
በፖለቲካውም ሆነ በምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚ) ግን
ባታ ረገድ ለውጭ ኤክስፐርቶች የልማት እርዳታና
እገዛ ለሚያደርጉ የዓለም መንግሥታት ትልቅ መተ
ማመኛ እና ዋስትና በመሆኑ ከላይ ከተገለጸው ጠቀ
ሜታ በተጨማሪ ለኢኮኖሚያዊ ግንባታም አማራጭ
የሌለው መስህብ ነው ።

የሀገራችንን ታሪክ አንድነት ፣ ሰላምና ብልጽግና ለሚሹ እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በዘመናዊ መልኩ ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አስተዳደርን ተቀብሎ ለታሪክ መከበር ለሰላምና ለኢኮኖሚ ብልጽግና ድርሻውን በማጤን ዘውድን በታላቅ የክብር ደረጃ ለማኖር ፍላጎታችንና ጥረታችን ነው ።

ይኸንንም ታሪካዊ የዘውድ ቅርሳችንን በስደት አገር ጠብቀው ያቆዩልን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ አምኃ ሥላሴንና ሌሎችንም እያመሰገንን ለአ ገራችን ክብርና ብልጽግና ሲባል በአስቸኳይ ወደ አገራችን እንዲመለሱልን ጥሪያችንን እናቀርባለን ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ አንድነቷ
ነጻነቷ ታሪኳና ቅርስዋ
ተጠብቆ ለዘላለም ትኑር ! ! !